ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)
Website: www.moreshwegenie.org E-mail: infoandpr@moreshwegenie.org

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ቅዳሜ መጋቢት ፲፫ ቀን ፪ሺህ፲፩ዓ.ም. ቅጽ ፮ቁጥር ፰

# 2011 ዓ/ም የሕዝብና የቤት ቆጠራ በተያዘለት የጊዜ ሠንጠረዥ ቢካሄድ ዓለም-አቀፋዊ መስፈርቶችን አያሟላም!

የሥነ-ሕዝብ ሞያተኞች እንደሚነግሩን በሕግ በተወሰነ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ቤት ለቤት እየተዞረ የሚካሄድ የሕዝብና የቤት ቆጠራ በአገር-አቀፍ ደረጃ ወሳኝ የሥነ-ሕዝብ ባሕሪያትን፣ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የቤቶችን መረጃ ለማግኘት የሚደረግ የግድና አስፈላጊ የሆነ ኹነት ነው። ይህ በበርካታ ቢሊዮኖን ብሮች የሚቆጠር የአገር ሀብት ፈሶበት የሚካሄደው የግድ አስፈላጊው የሕዝብና የቤት ቆጠራ እንዲካሄድና እንዲከወን መሟላት ያለባቸው ግድ የሚሉ ዓለም-አቀፋዊ ምቹ ሁኔታዎች አሉ። እነዚህ ዓለም-አቀፋዊ ምቹ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሚካሄድ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ተዓማኒነት ሊኖረው አይችልም። እነዚህ ዓለም-አቀፋዊ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፥

፩ኛ/ የሕዝብና የቤት ቆጠራውን የሚያካሂደው ተቋም ገለልተኛና ተዓማኒ መሆኑ መረጋገጡ ነው። በዚህ መስፈርት የኛን አገር የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን ገለልተኛነት ስንመረምር የተቋሙ ዋና ኃላፊ ቱግ ቱግ የሚሉ ብሔርተኛና የድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ሆነው እናገኛቸዋለን። በዚህ የኢትዮጵያ እውነት ተቅዋሙ ራሱን ከየትኛውም ወገን ለሚደርስበት ተጽእኖ ለማላቀቅ የሚቻልበት ተቋማዊ ሰውነት ሳይኖረው፤ የሕዝብና የቤት ቆጠራውን ማካሄዱ ከሚጠየቀው ዓለም-አቀፍ ምቹ ሁኔታ አኳያ ኢትዮጵያ ቆጠራውን ለማካሄድ ብቁ አይደለችም።

2ኛ/ ለሕዝብና ቤት ቆጠራው እንዲሰማሩ የሚታጩ ባለሞያዎች ሞያዊና ሥነ-ምግባራዊ ብቃታቸው ሙሉዕ ሆኖ መገኘት ነው። እንደሚታወቀው ዛሬ ኢትዮጵያ የምትገኘው በሽሚያ ፖለቲካ ውስጥ ነው። እያንዳንዱ ተፋላሚ ብሔርተኛ የሕዝብና የቤት ቆጠራውን ውጤት የሚፈልገው የፖለቲካ ግብ ለማስቆጠር የሚያስችለውን ሕግ ለማውጣት፣ ድንበር ለመስራትና ክልሌ የሚለውን ለማስፋት ነው። እነዚህን ዓላማዎች ታሳቢ አድርጎ የሚሰበሰብ የሕዝብና የቤት ቆጠራ መረጃ ተዓማኒነት የለውም። ስለዚህ፣ ቆጠራው በውጭ አገር ባለሞያዎች የበላይ መሪነትና ተቆጣጣሪነት እስካልተካሄደ ድረስ ሞያዊና ሥነ-ምግባራዊ ብቃታቸው ሙሉዕ ሆኖ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ቆጣሪዎችን ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ፣ ሞያዊና ሥነ-ምግባራዊ ብቃታቸው ሙሉዕ ባልሆኑ ቆጣሪዎች ዓለም- አቀፋዊ መስፈርቱን የሚያሟላ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ማድረግ አይታሰብም።

3ኛ/ ለሕዝብና ቤት ቆጠራው እንዲሰማሩ ከሚታጩ ባለሞያዎች ሞያዊና ሥነ-ምግባራዊ ብቃት ሙሉዕነት በተጨማሪ የቆጠራው ባለሞያዎች ቆጠራውን እንዲያከናውኑ ከሚጠቀሙበት ቴክኖሎጂ ጋር ያላቸው ትውውቅ ደረጃ ከፍተኛ መሆንና የቴክኖሎጂውን ጠንካራና ደካማ ጎን ጠንቅቆ ማወቅ ነው። የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ያለፉትን የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የተለያዩ ስህተቶች የተባሉትን ለማረም የዘንድሮው ቆጠራ ከወረቀት ስራ ውጭ በሆነ አኳኋን ሲ.ኤስ ፕሮ "CSpro" በተባለ ቴክኖሎጂ እንደሚካሄድ ነግሮናል።

ሆኖም ግን፣ ቆጠራውን ያካሂዳሉ የተባሉት መምህራን እንኳን ቴክኖሎጂው የሚጠይቀውን ከፍተኛ ደረጃ ትውውቅና ጠንካራና ደካማ ጎኑን ጠንቅቀው ሊያውቁ ይቅርና፤ ስለ ቴክኖሎጂው አጠቃቀም ለመምህራኑ ስልጣና የሚሰጡት የማዕከሉ ሰራተኞች ስለ ቴክኖሎጂው አጠቃቀም ፈረንጆቹ እየሰጧቸው ያለውን ስልጠና እንኳ በደንብ መረዳት ተስኗቸዋል።
ይህ ደግሞ ማዕከሉ ባካሄደው የናሙና ፈተና ታይቷል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ነው እንግዲህ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ቴክኖሎጂውን በቆጠራ ላይ በማዋሉ ብቻ ትክክለኛ ቆጠራ ማድረግ እንደሚቻል እያመነ ያለው።

## 2011 ዓ/ም የሕዝብና የቤት ቆጠራ በተያዘለት የጊዜ ሠንጠረዥ ቢካሄድ
## <u>ዓለም-አቀፋዊ መስፈርቶችን አያሟላም!</u>

ሆኖም ፣ እያንዳንዱ የቆጠራ ባለሞያ የቆጠራ ቴክኖሎጂው አጠቃቀሙ በደንብ ባልተረዳበት ሁኔታ የቆጠራ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ በመዋሉ ብቻ ዓለም-አቀፋዊ መስፈርቱን ያሟላ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ተደርጓል ለማለት የሚቻል አይደለም።

4ኛ/ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ተዓማኒ እንዲሆን ዓለም-አቀፋዊ መሟላት ያለበት መሥፈርት የሕዝብና የቤት ቆጠራው በትክክል እንዲካሄድ ቆጠራ በሚካሄድበት አከባቢና በዙሪያው ሰላምና ደኅንነት መረጋገጥ አለበት። በዛሬዋ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን መፈናቀል በታሪካችን አይተነውና ሰምተነው በማናውቀው ደረጃ የደረሰበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህም በመሆኑ የሕዝቡ መንፈስ የተረጋጋ አይደለም። እንደ ድሬዳዋ፣ ወልቃይትና ጠገዴ፣ ቤንሻንጉል እንዲሁም ራያ ባሉ የጦር ቀጠና በሆኑና በጉልበተኞች መዳፍ ስር በወደቁ አካባቢዎች ጦርኞቹ የኛ ዘር የሚሉትን ቁጥር ለመጨመርና የሌላውን ዘር በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ሕዝቡን እየቀወጡት ባሉበት ሁኔታ የቆጣሪዎች ዋስትናና ሰላም ተጠብቆ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ሊካሄድ አይችልም። የዘራቸውን ቁጥር ለመጨመር ከተሰለፉት ኃይሎች በተለይም ኦነጋውያን ሾልኮ የወጣው በሚስጥር ሲዞር የነበረ ማስረጃ እንደሚያስረዳው ይካሄዳል ተብሎ እየተጠበቀ ባለው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ኦሮሞ የሆኑ ቆጣሪዎች ሌሎች ነገዶች በተጽዕኖ ኦሮሞ ሆነው እንዲቆጠሩና ፈቃደኛ ካልሆኑ ደግሞ ቆጣሪዎቹ ቤቱን እንዲዘሉት ትዕዛዝ ተላልፏል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሌላ ዘሮች የተባሉት ዋስትናቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ እውነተኛ ዘራቸውንና ትክክለኛ ማንነታቸውን በሚካሄደው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ሊገልጡ አይችሉም።

አገዛዙም በየለቱ በሚቆጣጠረው ሜዲያ እንደሚነግረን የማይናቅ ቁጥር ያላቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች ማንነታቸው ባልታወቀ አማጽያን ቁጥጥር ስር እንደወደቁ እየሰማን ነው። በሌላ አነጋገር ቀላል የማይባሉ ቀበሌዎችና ወረዳዎች መንግሥት ነኝ ከሚለው አካል መዋቅር ውጭ ሆነ በታጠቁ ኃይሎች እየተዳደሩ ይገኛሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን መንግሥት ነኝ በሚለው ቁጥጥር ስር ያሉትም ቀበሌዎችና ወረዳዎች ፖለቲካው የተረጋጋ ስላልሆነና ሜዳው የሽሚያ ፍልሚያ የሚካሄድበት በመሆኑ የመንግሥት ተሿሚዎች ለየትኛው ተፋላሚ ኃይል እንደሚያገለግሉ በማይታወቅበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው። በዚህም አኳያ፣ አገሪቷ ወዴት እንደምትሄድ ስለማይታወቅና የትኛው ተፋላሚ ኃይል አሸንፎ እንደሚወጣ መናገር ስለማይቻል፤ ፍትጊያው ስላልለየለት ተራ ሕዝቡና ቆጣሪ ባለሞያዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ቆጠራውን የሚያስተባብሩት የመንግሥት ተሿሚዎች ጭምር ፍርሀት ውስጥ ሆነው አጠገባቸው ላለው ጉልበተኛ ታዛዥ በሆኑበት ሁኔታ ነው ያሉት። በዚህ የተነሳ፣ የተፋላሚ ኃይሎች የፖለቲካ ፍላጎት ማስፈጸሚያ እንጂ ዓለም-አቀፋዊ መሥፈርቱን የሚያሟላ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ማድረግ አይቻልም።

5ኛ/ ለሕዝብና ቤት ቆጠራው ዓለም-አቀፋዊ ምቹ ሁኔታ የሚቆጠረው ማኅበረሰብ ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጥ ስለሚካሄደው አጠቃላይ የሕዝብና የቤት ቆጠራ አስፈላጊነት ከአማካኝ በላይ የሆነ ግንዛቤ መኖር ነው። በእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ ግን ማኅበረሰባችን አስፈላጊው የሆነው ግንዛቤ ቢኖረው እንኳ፤ ሕዝቡን የሕዝብና የቤት ቆጠራውን ውጤት በምንፈልገው መንገድ ካልወሰድነው የምናስበውን የፖለቲካ ግብ ማሳካት አንችልም በሚሉ የተደራጁና የታጠቁ ተፋላሚ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በወደቀበት ሁኔታ ማኅበረሰባችን በሕይወት ለመቆየት ሲል በቁጥጥር ካዋሉት ኃይሎች የተለየ መረጃ ሊሰጥ አይችልም። ለምሳሌ ያህል፣ ራያ ብንሄድ ትግሬ ነኝ ካላልህ እንገልሀለን የሚል አገዛዝ አፍንጫው ላይ ተጭኖ፤ ወልቃይትም ብንወርድ አማራ ነኝ የምትል ከሆነ በሕይወትህ ፈርደህ ነው የሚል እስካፍንጫው የታጠቀ ፋሽስታዊ ኃይል በላዩ ላይ ተጭኖ፤ በአዲስ አበባ ጥያቄ ትርምስ እንዲሁም በመተከል ቤን ሻንጉል በሚታዩው መዋከብ ተጨባጭ ሁኔታዎች ውስጥ የራያ ፤ የወልቃይትና መተከልና አዲስ አበባ ሕዝብ ማንነቱን በትክክል እየተናገረ ሊቆጠር አይችልም። በዚህ ሁኔታ የሚካሄድ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ራያን መተከልን አዲስ አበባን ወልቃይትንና ሌሎችን «በሕግ» አሳልፎ ለመስጠት ካልሆነ በስተቀር ተዓማኒነት ያለው መረጃ ማግኘት ፈጽሞ አይቻልም።

6ኛ/ ዓለም-አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ለማድረግ ሌላው ቅድመ ሁኔታ ቆጠራው የሚካሄድበት መሣሪያ [Census Instrument] ግልጽ የሆነ፣ የማያሻማ፣ ነጠላና ያልተደረተ [mutually exclusive] የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦ መዘጋጀት ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ቆጠራው የሚካሄድበት መጠይቅ ሲያስተዋውቅ እንደተመለከትነው ለምሳሌ ማንነትን በተለመከተ አንድ መላሽ ኢትዮጵያዊ ብሎ አልያም በሚፈልገው ነገድ ስም ራሱን ገልጾ መመለስ እንዲችል ተደርጎ መጠይቁ መዘጋጀቱን ሲናገር ሰምተናል።
ይህ የመጠይቅ አዘገጃጀት ራሱን በቀዳሚነት ኢትዮጵያዊ ብሎ የሚገልጸውን የኅብረተሰብ ክፍል ለማግለልና በነገዱ እንዳይቆጠር አድርጎ አጠቃላይ አሐዙን ዝቅ ለማድረግ ታስቦበት በተለይም የዐማራውን ቁጥር እንዲቀንስ ለማድረግ በረቀቀ ተንኮል የተዘጋጀ ነው። የመጠይቁ አዘገጃጀት አጠቃላይ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ለማድረግ የሚዘጋጅ የቆጠራ መሳሪያ ሊኖረው

## 2011 ዓ/ም የሕዝብና የቤት ቆጠራ በተያዘለት የጊዜ ሠንጠረዥ ቢካሄድ
## <u>ዓለም-አቀፋዊ መስፈርቶችን አያሟላም!</u>

ከሚገባ ዓለም-አቀፋዊ መመዘኛ አኳያ የማያሻማ፣ ነጠላና ያልተደረቱ [mutually exclusive] የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወይንም ለአንድ ጥያቄ አንድ መልስ ለማግኘት ታስቦ መዘጋጀት አለበት የሚለውን መስፈርት የሚቃረን ነው። ለምን ቢባል፣ የአንድን የነገድ ማንነት በሚጠየቀበት ጥያቄ ላይ ኢትዮጵያዊ/ት የሚለው እንደ አንድ ምርጫ በምንም መስፈርት መቅረብ ስለማይችል ነው። ምክንያቱም ነገድ (ዐማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ አፋር፣ ሲዳማ ወዘተ...) የማንነት መገለጫ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊ/ት ግን የዜግነት መገለጫ በመሆኑ ነው። ለምን ቢባል፣ ማንነት አይቀየረም፣ አይለወጥም፤ ዜግነት ግን ይለወጣል፣ ይቀየራል።

7ኛ/ ሌላው ዓለም-አቀፋዊ ምቹ ሁኔታ በቆጠራው ሂደት የሚከሰት ማንኛውንም ችግር ባፋጣኝ የሚፈታበትና የሚያጋጥም ማንኛውም ዓይነት የኅብረተሰብ ቅሬታ ወዲያው ምላሽ ተሰጥቶ የሚስተካከልበት ሥርዓት መዘርጋት ነው። በኛ አገር ሁኔታ እንኳን እንደዚህ አይነት እስከታችኛው የማኅበረሰብ አደረጃጀት ድረስ የወረደ ሥርዓት ሊዘረጋ ይቅርና ቆጠራውን በሚያስፈጽመው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በየክልሉ ባሉ ቅርንጫፎችና ጣቢያዎች መካከል እንኳ የተዘረጋ እዚህ ግባ የሚባል ሥርዓት የለም።

8ኛ/ በመጨረሻ ደረጃ ተዓማኒነት ያለው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ለማድረጉ ተጠቃሽ የሚሆነው መስፈርት የቆጠራው ውጤት በጊዜው ይፋ መደረግ ነው። ሆኖም ግን፣ በፋሽስት ትገሬ-ወያኔ ዘመን በተካሄዱት ሁለት የሕዝብና የቤት ቆጠራዎች ከታየው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የኋላ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው የቆጠራው ውጤት እንኳን ዛሬ ሰላም በራቀበት ሁኔታ አንጻራዊ ሰላም በነበረበት ወቅት እንኳ ውጤቱ በጊዜው ይፋ አልተደረገም።

ለማጠቃለል ያህል፣ በ2010 ዓ/ም ሊካሄድ የነበረው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ያልተደረገው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባለፉት ጊዜያት በአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በዚህም የተነሳ የሰዎች ከመደበኛ መኖሪያቸው መፈናቀልና የፀጥታ መደፍረስን በዋነኝነት ጠቅሶ ሁለቱ የጋራ ምክር ቤቶች ቆጠራው እንዲራዘምለት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቦ በጠየቀው መሠረት እንዲራዘም በመፈቀዱ ነበር ቆጠራው ለ2011 ዓ/ም የተሸጋገረው። ሆኖም ግን፣ ዛሬ አገራችን ባለችበት ከፍተኛ የፖለቲካ አለመረጋጋትና መስቅልቅል፣ የኢኮኖሚ ውድቀትና ማህበራዊ ዝቅጠት ሁኔታዎች የጊዜ ሠንጠረዥ የተያዘለት የሕዝብና የቤት ቆጠራ ቢካሄድ ኖሮ ከላይ ከተራ ቁጥር 1ኛ እስከ 8ኛ የተጠቀሱትን ዓለም-አቀፍ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ምቹ ሁኔታ መሥፈርቶችን በምንም አኳኋን አያሟላም።

በጣም የሚያስገርመው፣ የአብይ አሕመድ መንግሥት እስከ ቅርብ ቀናት ድረስ ዐይኑን በጨው ታጥቡ አገራችን ያለችበትን አስከፊ የሕልውና ሁኔታዎችን በመካድ፤ የሕዝብና የቤት ቆጠራውን ለማካሄድ ቆርጦ ተነስቶ ነበር። ሆኖም ግን፣ አስከፊው ሁኔታ በጣም እያፈጠጠበት እና ሕዝባዊ ድጋፉ እየወደቀበት ሲመጣ፤ የ2011 የሕዝብና የቤት ቆጠራውን ላልተወሰነ ጊዜ ለማራዘም ተገዷል። አሁን አገራችን ባለችበት አጣብቅኝ የሕልውና ሁኔታ፤ እንኳንስ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ቀርቶ፤ ***ከአሁኑ ጀምሮ ነጋሪት የሚጎሰምበትና ጥሩንባ የሚነፋበት አገራዊ ምርጫ እንኳ እንደማይካሄድ ከወዲሁ መናገር ይቻላል።***

ሁሉም ዐማራ ለአንድ ዐማራ፤ አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ!
የዐማራ ሕዝብ በመራራ ትግሉ ኅልውናውንና ማንነቱን ያስከብራል!
ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል-ኪዳን ነው!